
# ዜና ልደታ

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!

በሦስተኛው ቀን



ከሙታን ተለይቶ ተነሳ

*በልደታ ለማርያም የኢ.ኦ.ተ. ቤተክርስቲያን እየተዘጋጀ የሚቀርብ ግንቦት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም (May, 2005)*


## *ማንን እንስማ ?*

በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በመስበክ ከሚያገለግሉ የወንጌል ሰባኪያን መካከል አንዱ የሆኑት አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ናቸው። አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ከሃያ ዓመት ላላነሰ ጊዜ በስብከተ ወንጌል በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በተለይም ላለፉት አስራ ሦስት ዓመታት በሰሜን አሜሪካ ግዛቶች እና በአውሮፓ በመዘዋወር ወንጌልን በመስበክ ላይ ይገኛሉ። ከሰባ በላይ የሆኑ የአባ ወልደ ትንሣኤ የወንጌል ስብከቶች በካሴት እየተባዙ በኢትዮጵያ ፥ በአፍሪካ ፥ በአውሮፓና በአሜሪካ በመሰራጨት ወንጌል በመላው ዓለም እንዲስፋፋ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ መነሻው ባልታወቀ ምክንያት እኚህ አባት ከቤተክርስቲያን ተወግዘው እንደተለዩ ተደርጎ ሕዝቡን ግራ የሚያጋባና የሚከፋፍል የሐሰት ወሬ እየተናፈሰ ይገኛል።

የዝግጅት ክፍላችን በዚሁ ርዕስ ዙሪያ እውነቱን ለመረዳትና ለሕብረተሰባችን ትክክለኛውን መረጃ ለማቅረብ ወደ ብፁዐን አባቶች ጥያቄያችንን በማቅረብ ያገኘነውን መልስ ይዘን ቀርበናል።

*አባ ወልደ ትንሣኤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዘዋል?* በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ያነጋገርናቸው።

1. ***ብፁዕ አቡነ ማትያስ*** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን አሜሪካ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ።
   <u>*ከዋሽንግተን ዲሲ*</u>

2. ***ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ*** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ እና በከምባታ ጉራጌ ሃዲያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ።
   <u>*ከአዲስ አበባ*</u>

3. ***ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ*** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና በአዲስ አበባ የቅድስት ሥላሴ ከፍተኛ ቴዎሎጂ ኮሌጅ ዋና ሃላፊ (ዲን)።
   <u>*ከአዲስ አበባ*</u>

4. ***ብፁዕ አቡነ ገብርኤል*** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ።
   <u>*ከቨርጂንያ*</u>

ሲሆኑ ብፁዐን አባቶች የዝግጅት ክፍላችን ላቀረበላቸው ጥያቄ በፍፁም ፈቃደኝነት ስለሰጡን መልስ ከልብ እያመሰገንን። የሰጡንን መልስ <u>*በገጽ 3*</u> አቅርበነዋል።

(Please Continue on to the next page)

(This part continues after page Two)

## ማንን እንስማ ? ከገጽ 3 የዞረ

በአንድነትና በመተሳሰብ ልዩነትንና አለመግባባትን ለማቻቻል መሞከርና ስህተት አለ እንኳን ቢባል ለመተራረምና ለመማማር መነሳቱ የተሻለ ይመስለናል።

<u>*የተከበራችሁ አንባቢያን የብፁዐን አባቶችን መልስ አንብበናል። ስለ ውግዘትም ግንዛቤ አግኝተናል። ታዲያ ማንን እንስማ? አባቶችን? ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን? ወይስ... ?*</u>

# ማንን እንስማ?

ከገጽ 1 የዞረ

በመጀመሪያ ያነጋገርናቸው በሰሜን አሜሪካ ሀገረ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የሆኑትን ብፁዕ አቡነ ማትያስን ነበር። ብፁዕነታቸው ጥያቄያችንን በደስታ በመቀበል የሰጡን መልስ የሚከተለው ነው።

*ዜና ልደታ* ~ በቅድሚያ የብፁዕነትዎ ቡራኬ ይድረሰን። እዚህ በአካባቢያችን አባ ወልደ ትንሣኤ በቤተክርስቲያን ተወግዘዋል እየተባለ በሰፊው ይነገራል። እርስዎ በዚህ በሰሜን አሜሪካ ሀገረ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ እንደመሆንዎ መጠን ይህንን በተመለከተ ያለዎትን አስተያየት ቢገጹልን?

*ብፁዕ አቡነ ማትያስ* ~ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያስተላልፈው ማንኛውም ውሳኔ በመላው ዓለም ለሚገኙ ሀገረ ስብከቶች ይተላለፋል። ከዚህ አንጻር አባ ወልደ ትንሣኤን በተመለከተ ቅዱስ ሲኖዶስ ያስተላለፈው ምንም ዓይነት ውግዘት አልደረሰኝም። በአጠቃላይ አባ ወልደ ትንሣኤን በተመለከተ ኦፊሲያሊ የሰማሁት ነገር የለም።

*ዜና ልደታ* ~ በቅዱስ ሲኖዶሱ አልተወገዙም ማለት ነው?



ብፁዕ አቡነ ማትያስ ሊቀ ጳጳስ ከዋሽንግተን ዲሲ

*ብፁዕ አቡነ ማቲያስ* ~ ከዚህ ቀደምም ተመሳሳይ አስተያየቶች ሰምቼ ስለነበር ወደ አዲስ አበባ በመደወል የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከሆኑ ብፁዓን አባቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአባ ወልደ ትንሣኤ ላይ ምንም ዓይነት ውግዘት አለማስተላለፏን ለመረዳት ችያለሁ። በዚህ ጉዳይ ተጨማሪ ማብራሪያ ከብፁዕ አቡነ ገብርኤል ልታገኝ ትችላለህ። አስፈላጊ ከሆነም ወደ አዲስ አበባ በመደወል መጠየቅም ይቻላል።

*ዜና ልደታ* ~ ብፁዕነዎት ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን።

*ብፁዕ አቡነ ማትያስ* ~ እግዚአብሔር ይባርክህ አገልግሎትህን ሁሉ ይባርክልህ።

*ዜና ልደታ* ~ አሜን!

ይህንንው ጉዳይ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት ወደ ኢትዮጵያ በመደወል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከሆኑት ብፁዐን አባቶች መካከልም አነጋግረን ነበር። በቅድሚያ ያነጋገርናቸው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና እና የከምባታ ጉራጌ ሃዲያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስን ነበር። ወደ ብፁዕነታቸው በመደወል በፀሐፊያቸው አማካንነት አግኝተናቸው ቡራኬያቸውን ከተቀበልን በኋላ ከየት እንደደወልን በመግለጽ ቀጥታ ወደ ጥያቄያችን ነበር የገባነው።

*ዜና ልደታ* ~ ብፁዕ አባታችን እዚህ በሰሜን አሜሪካን አካባቢ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዘዋል እየተባለ ይነገራል። በትክክል ተዋግዘው ከሆነ መቼና በምን ምክንያት እንደተወገዙ ቢገልፁልኝ



ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ከአዲስ አበባ

*ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ* ~ ማን ነው ተወገዙ ያለው?

*ዜና ልደታ* ~ እዚህ በዋሽንግተን አካባቢ ተወግዘዋል ተብሎ በሰፊው ስለሚነገር ይሄንንው ለማረጋገጥ ነበር የደወልነው?

*ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ* ~ አልተወገዙም መወገዛቸውን እኔ አላውቅም።

*ዜና ልደታ* ~ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አልተወገዙም ማለት ነው?

*ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ* ~ አልተወገዙም! አልተወገዙም! ያወገዛቸው የለም።

*ዜና ልደታ* ~ ብፁዕነትዎ ስለሰጡን ምላሽ ከልብ አመሰግናለሁ።

በመቀጠል ያነጋገርናቸው ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና በአዲስ አበባ የቅድስት ሥላሴ ከፍተኛ ቴዎሎጂ ኮሌጅ ኃላፊን ነበር። በተመሳሳይ ወደ አዲስ አበባ በመደወል የብፁዕነታቸውን ቡራኬ ከተቀበልን በኋላ ወደ ጥያቄያችን በመተላለፍ ፦

*ዜና ልደታ* - ብፁዕ አባታችን አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን ያውቋቸዋል?

*ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ* - እሄ ኮሌጁ የነበሩት?

*ዜና ልደታ* - አዎ እሳቸው እዚህ በሰሜን አሜሪካን አካባቢ በቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዘዋል እየተባለ ይነገራል።



ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ሊቀ ጳጳስ ከአዲስ አበባ

*ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ* - እንዴ ለምንድን ነው የሚወገዙት ምን አደረጉ እና ነው?

*ዜና ልደታ* - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዟቸዋል እየተባለ በሰፊው ይወራል?

*ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ* - ወንድሜ በምንም ዓይነት አባ ወልደ ትንሣኤ እንኳን ሊወገዙ ስማቸው እንኳን ጨርሶ ጨርሶ ተነስቶም አያውቅም። እንደውም ወደ እዚያ (ወደ ውጪ ሀገር) ሄደው ነው እንጂ ለጵጵስና ታጭተው ነበር። አባ ወልደ ትንሣኤ እውነተኛ ሐዋርያ ናቸው። መንፈሳዊ ኮሌጁን ለማሳደግ ብዙ የሚጥሩ ፣ እዚህ ኮሌጅ ሳሉ የተመሰገኑ ፣ ስብከታቸው ሕዝቡ የሚወደው ፣ እንደውም አዲስ አበባ ያለው ሕዝብ የእሳቸውን ካሴት ነው ሲሰማ ነው የሚውለው።

*ዜና ልደታ* - ብፁዕነትዎ ስለሰጡን አስተያየት በጣም እናመሰግናለን።

*ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ* - እግዚአብሔር ይባርክህ!

*ዜና ልደታ* - አሜን።

በመጨረሻም በዚህ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጡን ጥያቄያችንን ያቀረብንላቸው ለብፁዕ አቡነ ገብርኤል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ነበር።

*ዜና ልደታ* ~ ብፁዕ አባታችን እዚህ በሰሜን አሜሪካን ከሚገኙት የወንጌል መምህራን መካከል አንዱ የሆኑት አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በቅዱስ ስኖዶስ ተወግዘዋል እየተባለ በሰፍው ይነገራል። ስለዚህ ጉዳይ ብፁዕ አባታችን አቡነ ማትያስን አነጋግረን ተጨማሪ ማብራሪያ ከእርሶ እንደምናገኝ ጠቁመውን ነበር። ብፁዕነትዎ ቢገልጹልን።

*ብፁዕ አቡነ ገብርኤል* ~ በመጀመሪያ ስለ ውግዘት ትንሽ ገለጻ መስጠት ያስፈልጋል። ውግዘት ማለት ከባድ የሆነ ነገር ነው። በሃይማኖታዊ አገላለፅ በተለይም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት አገላለፅ ቅኖናን ያፈረሰ እና ሃይማኖት የካደ ከምእመናንና ከቤተክርስቲያን የሚለይበት ታላቅ መንፈስ ቅዱሳዊ መሣሪያ ነው። አንድ ሰው ቅኖና አፈረሰ ተብሎ ተከሶ ሲቀርብ ይጠየቃል ፣ እምነት ክህደት ይሰጣል ፣ የለም ተሳስተሃል ተመለስ ይባላል እንቢ ካለ ነው የሚወገዘው። በሃይማኖት በኩልም እንደዚሁ ሳይቀርብ ፣ ሳይጠየቅ ፣ እምነት ክህደት ሳይሰጥና ቃሉ ሳይታወቅ በማዶ አይወገዝም። ቢወገዝም "ዘእወግዝ በከንቱ ፍቱሕ ውእቱ" (ያለ አግባብ በከንቱ ያወገዘ ውግዘቱ የተፈታ ነው) የሚባለው ይሄ ነው።

አባ ወልደ ትንሣኤ ቅኖና አፍርሰው አልተወገዙም አልተወቀሱም። ሃይማኖት ለውጠውም አልተከሰሱ። በሲኖዶስ በኩል አባ ወልደ ትንሣኤ እንኳንስ ውግዘት ወቀሳም ደርሶባቸው አያውቅም። ሰምተንም አናውቅም።

አባ ወልደ ትንሣኤ በሲኖዶስ በሙሉ ሊቃነ ጳጳሳቱ የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸው መነኩሴ ናቸው። እሳቸውን በተመለከተ እንኳን ውግዘት ክስና ወቀሳ እንኳን ቀርቦ አያውቅም።



ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ ከቨርጂንያ

እዚህ አገር ከመጣሁ ጀምሮም በየአስራ አምስት ቀኑ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ብፁዐን አባቶች ከብዙዎቹ ጋር እገናኛለሁ። እኔ ወደዚህ ከመጣሁም በኋላ በሲኖዶስ ስለ አባ ወልደ ትንሣኤ አንዳችም ወቀሳ ደርሶ አያውቅም። በዚህ አካባቢ ግን ብዙ የሐሰት ወሬ ይወራል። እንዲህ ዓይነት የሐሰት ወሬ ማውራት ደግሞ ተገቢ አይደለም። ሲኖዶስ ያላወገዘውን ሲኖዶስ አውግዟታል ማለት ሲኖዶስን ሐሰተኛ ማድረግ ይመስለኛል።

ለምሳሌ ~ አሪዮስ ቀርቦ ተከራክሮ አልመለስም ስላለ ነው በኒቂያ በ325 ዓ.ም የተወገዘው። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ሕፁፅ ነው ብለው የተናገሩት መቅደንዮስና ተከታዮቹ ቀርበው ተከራክረው በክህደታቸው ስለጸኑ ነው የተወገዙት። ንስጥሮስም ቀርቦ ተጠይቆ ከፍተኛ ክርክር አድርጎ አልመለስም ስላለ ነው የተወገዘው። እናም ውግዘት እንዲሁ በማዶ አይሆንም። ውግዘት እንዲሁ በቀላሉ የሚሰነዘርና የሚደረግ አይደለም። ስለዚህ የተነገረው ሁሉ ከእውነት የራቀ ነው።

*ዜና ልደታ* ~ ብፁዕ አባታችን ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን።

*ብፁዕ አቡነ ገብርኤል* ~ ልጆቼ እናንተም ስለ ቤተክርስቲያናችሁ መቆርቆራችሁ እጅግ መልካም ነው። እውነትንም እውነትን ላላወቁ ለማሳወቅ የምታደርጉት ጥረት ድንቅ ነውና እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

*ዜና ልደታ* ~ አሜን።

በአጠቃላይ ከብፁዐን አባቶቻችን እንደተረዳነው በአባ ወልደ ትንሣኤ ላይ በቅዱስ ሲኖዶስ በኩል ምንም ዓይነት ውግዘትም ሆነ ክስ ያለመኖሩን ነው። እውነታው ይህ ከሆነ አባ ወልደ ትንሣኤ ተወግዘዋል የሚለው አባባል ከየት መጣ? ውግዘት እንዲሁ በማንም የማይሰጥ ስለመሆኑና በቤተክርስቲያኒቱ ቅዱስ ሲኖዶስ በከፍተኛ ደረጃ ውይይት ተደርጎበት በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት የሚተላለፍ እንደሆነ ካወቅንና አባ ወልደ ትንሣኤ በቅዱስ ሲኖዶስ አለመወገዛቸውን ከተረዳን። እንግዲህ እንዲህ አለ ከምንልና በስማ በለው የንግግር ጫፎችን ይዘን ከማማትና ከመፍረድ ሙሉውን ሰምተን ግራ ቀኙን ጠይቀን እንረዳ። ከመለያየት ፣ ከመተቻቸት ፣ ከመጠላለትና ከመካሰስ ይልቅ እንደ እግዚአብሔር ቃል በፍቅር ፣

በገጽ 9 ይቀጥላል